# <u>የግንቦት7 ንቅናቄ ምንድነው? ምንስ አመጣው? ምንስ ሊያመጣ ይፈልጋል?</u>[1]

በቅድሚያ ግንቦት7፣ የፍትህ፣ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ለመጀመሪያ ግዜ በለንደን ላይ የጠራውን ስብሰባ ለመሳተፍ እዚህ በመገኘታችሁ በአክበሮት አመሰግናችኋለሁ፡፡

በዛሬው እለት ለውይይታችን መንደርደሪያ እንዲሆን የማቀርበው ሃሳብ በሶሰት ቦታ የተከፈለ ነው፡፡ ክፍፍሉ ጥብቅና የማይፋለስ ግን አይደለም፡፡ እንደ ሁኔታው እንደ አስፈላጊነቱ ወጣ ገባ አያልኩ የምሄድበት ክፍፍል ይሆናል፡፡

የመጀመሪያው ክፍል ግንቦት ሰባት ምን እንደሆነ? ለምን እንደመጣ? ምን አላማ እንዳላውና ለምን ይህን አላማ ማሳካት ይቻላል? የሚል እምነት እንደያዘና ሌሎችንም ተመሳሳይ ጉዳዮች የሚነካ ይሆናል፡፡

በሁለተኛው ክፍል ግንቦት7 እና ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች ምን አይነት ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል የሚለውን ጥያቄ በማንሳት ምላሹን ለመስጠት እሞክራለሁ፡፡

ሶስተኛው ደግሞ፣ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ማንኛውም ሃገር ወዳድ ዜጋ ዛሬ ሀገራችንና ሁላችንም በምንገኝበት እጅግ አሳዛኝና ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ሊሸከም የሚገባው ሃላፊነትና የስራ ድርሻ ምን መሆን አለበት የሚለውን  ጥያቄ በማንሳት በአጭሩ ምላሽ መስጠት ይሆናል፡፡

ከመጀመሪያው ልጀምር፡፡ ግንቦት 7 ምን እንደሆነ ከመናገሬ በፊት ምን እንዳልሆነ መናገሩ ከብዙ ብዥታዎች ይገላግለናል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ይህ አቀራራብ ትኩረታችንን በተወሰነ ደረጃ በጠሩና ነገር ግን የበለጠ መጥራት በሚገባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች እንዲያነጣጥር በማድረግ ውይይታችንንም ትርፋማ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ አንድ አንዴ አንድ ነገር እንዲህ ነው ከማለት፣ እንዲህ አይደለም በማለት በሚደረግ ገለጻ በጉዳዩ ላይ የተሻለ ግንዛቤ እንድናገኝ ማድረግ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ንግግሬን ግንቦት7 ምንድን ነው ሳይሆን ምንድነው ያልሆነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ በመስጠት እጀምራለሁ፡፡ አደራ የምለው ቀጥዬ የማቀርባቸውን ጭብጦች ልብ እንድትሉልኝ ነው፡፡

ግንቦት7 በቅንጅት አመራር መሃከል ወይም በድርጅቱ ውስጥ የተነሳው ውዝግብ ውጤት አይደለም፡፡

ግንቦት7 ቅንጅት ሲከፋፈል አንዱ ክፋይ ሆኖ የወጣ አካል አይደለም፡፡ ቅንጅት የተከፈለው ሁለት ቦታ ነው፡፡ ከእዚህ ውጭ ያለው ቅንጅት የመለስ ዜናዊ የመመራው የአየለ ጫሚሶን ቅንጅት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቅንጅት ነው የሚል እምነት አንደማይኖራችሁ አውቃለሁ፡፡

ቅንጅት የተከፈለው ሁለት ቦታ ነው ስል፣ ስለ እኩል ክፍያ አይደለም የማወራው፡፡ አሁን እራሱን አንድነት ብሎ የተደራጀው በወይዘሪት ብርቱካን በሚመራውና  በኤንጂኒየር ሃይሉ ሻውል በሚመራው እራሱን ምን ብሎ እንደሚጠራ፣ በእውነት ነው፣ በማላውቀው ሌላ ቡድን ብቻ መከፈሉን ለመግለጽነው፡፡

---

[1] ጁን 22 2008፣ ግንቦት7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ እራሱን ለማስተዋወቅ በለንደን ላይ በጠራው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ከቀረበው ንግግር የተወሰደ፡፡

ግንቦት ሰባት በቅንጅት ውስጥ ምንም አይነት ውዝግብ ባይነሳም መፈጠሩ የማይቀር እንቅስቃሴ ነበር። የግንቦት 7 እንቅስቃሴ መፈጠር ዋናውና ብቸኛው ምክንያት በቅንጅት ውስጥ የነበርን ጥቂት ግለሰቦች በመለስ ዜናዊ ግፈኛ አገዛዝ ምንነትና ይህንን አገዛዝ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ ለማንሳት በስራ ላይ መዋል ስላለበት የትግል ስልት የደረሰንበት ከቅንጅት የተለየ ግንዛቤ ነው። ይህ ግንዛቤ ቅንጅት ይዞት ከቆየው እምነት ጋር የሚቃረን በመሆኑ ሁላችንም ተስማምተን በገባንበት የቅንጅት የህጋዊና የሰላማዊ የፖለቲካ መድረክ ላይ ምክክር እናድርግበት ማለት አይቻልም ነበር። በእዚህ ጉዳይ በቅንጅት ውስጥ ወይይት የተደረገበት፣ ልዩነትም የተፈጠረበት ወቅት አልነበረም።

ይህ ማለት ግለሰቦች ቢያነሱት ይከለከሉ ነበር ማለት አይደለም። ነገር ግን ለቅንጅትም፣ ለራሱ ጉዳዩን ለሚያነሱት ወገኖችም ሆነ በእዚህ ጉዳይ ላይ ለመምከር ፍላጎቱ የማይኖራቸውን የአመራር አባላት አደጋ ላይ የሚጥል ይሆን ነበር። በሌላ በኩልም ሁላችንም ተስማምተን የገባንበትን የፓርቲውን የጨዋታ ህግ እኛ አልተስማማንም ቀይሩልን ብሎ ጭቅጨቅና አምባጓሮ ማንሳት ፍትሃዊም ሞራላዊም አይሆንም ነበር።

በመሆኑም ከቅንጅት መሰረታዊ የድርጅቱ የመታገያ እምነቶች ውጭ ለመሄድ የፈለግን ግለሰቦች በቅንጅት ውስጥ ውዝግብ ተነሳም አልተነሳም ለማራመድ በፈለግነው የተለየ የትግል ሰልት  የተነሳ ከድርጅቱ መልቀቃችን አይቀርም ነበር።

እንዲህም ሆኖ፣ ለመልቀቅ ያሰብነው ግለሰቦች ፍላጎትና እምነት ቅንጅትን በምንለቅበት ወቅት ከድርጅቱ ጋር ጠብ ስላለን እንዳልሆነ፣ ባላንጣዎቻችንም ‹እዩዋቸው ተጣሉ! ተሰነጣጠቁ! › የሚል ማላገጫ ሳያደርጉን፣ በሃገራችን ላይ እንዲሰፍን በምንፈልገው ዴሞክራሲያዊ ስርአት ላይ ሁላችንም የቅንጅት ቤተሰቦች ምንም ልዩነት የሌለን መሆኑን፣ ነገር ግን ልዩነቱ እኛ ከቅንጅት የተለየ የትግል ስልት ያስፈልጋል የሚል እምነት ሰላለን ብቻ ቅንጅትን ጥለን መሄዳችንን ለሁሉም ግልጽ እንዲሆን ነበር።

በሌላ በኩልም እኛ ከመውጣታችን በፊት በመለስ ዜናዊ ግድያና አፈና በብዙ መልኩ ተዳክሞ የነበረውን ቅንጅት በእግሩ እስኪቆም ድረስ የቻልነውን በማገዝ፣ በተለይ በድርጅቱ ውስጥ ከእስር ቤት ጀምሮ ሲያመረቅዝ የነበረውና መሪዎቹ ከእስር ሲፈቱ የፈነዳው፣ በዴሞክራሲያዊ ድርጅት ምንነትና በዴሞክራሲያዊ አመራር ዙሪያ የተነሳው ችግር የሚመለከተን በመሆኑ ይህን እልባት ማስያዝ ሃላፊነት ያለብን መሆኑን ተረድተን ነበር። በእኛ እምነት ምንም እንኳን በመለስ ዜናዊ ፈቃድ፣ መለስ ዜናዊ ህግና ህገ-መንግስት ሆኗልና፣ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች በፖለቲካ መድረኩ ላይ እርባና ያለው ስራ እንዲሰሩ እድል ያገኛሉ ብለን ባናምንም፣ ለክፉም ለደጉም የቅንጅት ባልደረቦቻችን የሚንቀሳቀሱበትን አሸቸጋሪና ውስብስብ ሁኔታ እስከተረዱ ድረስ መጠናከራቸውን የፈለግነው ነበር። አሁንም ቢሆን ከእዚህ የተለየ ፍላጎት የለንም።

ይህ ፍላጎታችን በፈለግነው ፍጥነት ቅንጅትን ጥሎ ለመውጣት እንዳንችል አድርጎናል። በተለይ ደግሞ ይህንን የኛን የተለየ የትግል ስልት አዝማሚያ የሚያውቁ አንዳንድ የድርጅቱ መሪዎች የእኛ ከድርጅቱ መውጣት በድርጅቱ ላይ ጉዳት ያመጣል የሚል ስጋት ስለነበራቸው ይህንን ስጋታቸውን ረግጠን ለማለፍ የሚቻል አልነበረም። ይህ ቀላል ያልነበረ ተጽእኖ  በፈለግነው ፍጥነት ቅንጅትን ለቀን ለመውጣትና ወሳኝ ነው ብለን ባሰብነው የትግል አቅጣጫ እንቅስቃሴ እንዳናደርግ አግቶ አቆይቶናል።

ውሎ አድሮ ግን፣ የመለስ አገዛዝ አፈናና ግፉ የማያባራ ሳይሆን ማለቂያ የሌለው እየሆነ ሲታይ፣ ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ማድርግ ለሚፈልጉ የፖለቲካ ድርጅቶች ምንም መፈናፈኛ ለመስጠት ቅንጣት ፍላጎት እንደማይኖረው ምንም ተጨማሪ መረጃ የማያስፈልግ ሲሆን፣ ህዝብና ሃገርን እየጎዳ የሚሄድበት ፍጥነት እየጨመረና አሳሳቢ እየሆነ ሲማጣ፣ ይህን በእብሪት የተሞላ አገዛዝ በሃገራችንና በሁላችንም ላይ የሚፈጽምው ሁለገብ ወንጀል ለመቋቋም መስራት የሚገባውን ሳንሰራ የምናጠፋው እያንዳንዱ ደቂቃ ራሳችንን ተጠያቂ ያደርገናል የሚል ስጋት ውስጥ ጨመረን።

ከእዚህ በተጨማሪ በቅንጅት ውስጥ የተነሳውን መከፋፈል ስልጡን በሆነና መሰረታዊ የዴሞክረሲ መርሆችን በተከተለ መንገድ ለመፍታት ያለው እድል እየመነመነ መጣ።

እኛም በቅንጅት ውስጥ ተቀምጠን አልፎ አልፎ በንግግርም ይሁን በጽሁፍ የመለስን መንግስት ምንነትና እርሱን ለመታገል አስፈላጊ ናቸው በምንላቸው ጉዳዮችና ስልቶች ላይ የምንሰጠው አስተያየት፣ በቅንጅት ውስጥ በመቆየታችን ከምንሰጠው ጥቅም የበለጠ ጉዳት የሚያመጣ፣ በባልደረቦቻችንም ላይ አደጋ የሚያስከትል መሆኑን እኛ ብቻ ሳንሆን ባለደረቦቻችንም የተረዱበት ደረጃ ላይ ደረስን። አርፋችሁ የማትቀመጡ ከሆነ አንደኛውኑ እራሳችሁን ብታገሉልን የሚል መልእክት መሳይ ነገርም ይደርሰን ጀመር። ብዙ ስራዎች ልንሰራ እንችልባቸው የነበረውን ወርቃማ ግዚያት ካባከንን በኋላ በመጨረሻ የተወሰንነው እራሳችንን ከቅንጅት አገልለናል። ልብ በሉ ከቅንጅት ተከፍለን ወጥተናል አላልንም። እራሳችንን አግለላን ነው ያልነው። ግንቦት7 ማቋቋማችንን ይፋ አድርገናል። ይህን ካልኩ የግንቦት7ን ምንነት ወደሚመለከተው ነጥብ ልሽጋገር።

## ከእዚህ ቀጥዬ ግንቦት ሰባት ምነድነው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እሞክራለሁ።

ግንቦት ሰባት ከመቋቋሙ በፊት ለመቋቋሙ ምክንያት የሆኑትን ምክንያቶች በተለያዩ ሰነዶች አስቀምጧል ከእነዚህ ሰነዶች ዋንኛው። **የ1997 ምርጫና ከምርጫ በኋላ የነበረው ትግል ግምገማ** የሚለው ሰነድ ነው።

ይህ ሰነድ በመግቢያው ላይ፣ የ1997 ምርጫ የነበሩት በጎ ገጽታዎችና ያምርጫ ግልጽ ያደረጋቸው የፖለቲካ ጭብጦች በስፋት ይዳስሳል። በአጭሩ ግን እንዲህ በማለት ይደመድማል።

ሁኔታዎች ቢመቻቹ ዘመናዊና ስልጡን ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት እንዲመሰረት የሚያስችል ሁኔታ በሃገራችን አለ። ይህ ሁኔታ በዋንኛነት ህዝቡና የፖለቲካ ድርጅቶች በምርጫ 97 ወቅት ባሳዩት ብስለትና ብቃት የተረጋጋጠ ነው። ይላል

**ሰላማዊ ትግሉ የተመረጠባቸው ምክንያቶች ሲያትት፤** ሰለማዊ ትግል በቅንጅት ወስጥ እንደ ብቸኛ ሳይሆን እንደዋንኛ አማራጭ የተወሰደ መሆኑን በመጠቆም፣ ቅንጅት እንደ ተቋምም ቢሆን ሰላማዊ ትግል ብቸኛው የትግል አማራጭ አድርጎ የሚያይ ተቋም አድርጎ መውሰድ ስህተት ይሆናል ይላል። ስለሰላማዊ ትግሉ የቅንጅቱ መሪዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች እጅግ በከረረ ቋንቋ አማራጭ የሌለው ስልት አድርገው በሚያስቀምጡበትም ሰአት ቢሆን ይህ ስልት እንደ ቀኖና የማይነቃነቅ አድረገው የሚያዩት የድርጅቱ መሪዎች ጥቂቶች ነበሩ። በቅንጀት ውስጥ በማናቸውም ግዜና ሁኔታ ሰላማዊ የትግል ስልት አማራጭ ዋንኛው አማራች ብቻ ሳይሆን ብቸኛው አማራጭ ነው የሚሉ ግለሰቦች በአንድ እጅ ጣት ቁጥር እንኳን የሚደርሱ አልነበሩም። ነግር ግን ዋንኛው አማራጭ አድርገው የሚያዩትም ሳይቀሩ ሰላማዊ ትግሉ እንዲሰራ ከተፈለገ በግማሽ ልብ የማይገባበት እንደሆነ ተስማምተው የገቡበት ጉዳይ ነበር።

ሰላማዊ ትግል እንዲሰራ ከተፈለገ ላይሰራ ይችላል የሚል ጥርጣሬ እየነዙ ወይም ይዘው መንቀሳቀስ አግባብብነት አይኖረውም የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረስ ይህንን የትግል ስልት በሙሉ ልብ፣ በነበረው አጋጣሚ መሞከር የግድ ይል ነበር፡፡ በነበረው ሁኔታ ሌላ አይነት የትግል አማራጭ እንደሚኖር አድርጎ ማስቀመጥ አደጋ ነበረው፡፡ ውሎ አድሮም ሰላማዊ ትግልን በሚመለከት አማራጭ የሌለው አካሄድ ነው ብላችሁ ነበር የሚል ክስ ያስከተለው የአንዳንዶቹ መሪዎች አበባል ሳይቀር መነሻው ይህንን ትግል ከልባችን እንድነገባበት በማሰብ የተሰነዘሩ ንግግሮች በወቅቱ የቆሙበትን አመክኗዊ መሰረት ካለመገንዘብ ነው፡፡ በሰላማዊ መንገድ መታግል በማያቻልበት ወቅት ሌላ የመታገያ ስልት ከመፈለግ ይልቅ ከሰላማዊ ትግሉ ጋር የተገባውን የቁርባን ጋብቻ ሳይሰብሩ በባርነት መኖር የሚል አማራጭ በቅንጅት መድረክ ተነስቶም አያውቅም፡፡ ቅንጅትም እንዲህ አይነት ድርጅት አልነበረም፡፡

ከላይ የተባለው እንዳለ ሆኖ የግመገማው ሰነድ ቀጥሎ የተመለከተው ጉዳይ በወቅቱ ሰላማዊ የሆነውን የትግል ስልት ቅንጅት እንዲመርጥ ያደረጉትን ምክንያቶች ነው፡፡ እነዚህንም በአጭሩ እንዲህ ይላቸዋል፡፡

- አነስተኛ የህይወትና የንብረት ዋጋ የሚያስከፍል በመሆኑ፤
- የገጠመን ባላንጣ ጥንካሬው በጠመንጃ በመሆኑ፣ ይህንን ባላንጣ በጠመንጃ መግጠም በጥንካሬው መግጠም ይሆናል፡፡ እንዲህ አይነቱም በጠመንጃ መታግል የለመደን ሃይል በአግባቡ መታግል የሚቻለው በማያውቀውና ግራ በሚያገባው ሰላማዊ ትግል መሆኑ፤
- ጠመንጃ ተሸናፊና አሸናፊ፣ ቂምና ቁርሾ ይዞ ይመጣል፡፡ ለሰላምና ለመረጋጋት የሚጠቅመንን ሁሉንም አሸናፊ አድርጎ የሚያቀርብ ሁኔታ አይፈጥርም፡፡ ተሸናፊዎች አዲስ ተከፊዎች ሆነው፣ ተረኛ አማጺ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ይህ ከሆነ የአመጽ አዙሪት አያበቃም፡፡ መከራችንም አያልቅም፡፡

በምርጫ 97 ወቅት ለሰለማዊ ትግል ጠቀሜታ ቅንጅት የሰጣቸው ወንኛ ምክንያቶች እነዚህ ነበሩ፡፡ ቀጥሎ ያደረግነው ግምገማ እነዚህ ምክንያቶች ከመርጫ 97 በኂላ የነበራቸው ትርጉም ምን እንደሚመስል ነበር፡፡

**ህወሀት/ኢህአዴግ ከምርጫ 97 በሁዋላ የወሰዳቸው እርምጃዎችና ሰላማዊ ትግል፤**

- ማጭበርበር፣ ለሰላምና ለእርቅ ሲባል የቀረበለትን የብሄራዊ አንድነት መንግስት ሃሰብ አለመቀበል፤ ይህም ቀርቶ ከነሰረቅኸው ድምጽ በስልጣን ቀጥል ነገር ግን መጪ ምርጫዎች እንደ97ቱ ምርጫ ችግር እንዳይገጥማቸው መከላከያ የሚሆኑትን የነጻ ተቋማት ምስረታ ሃሳብ እንዲቀበል የቀረበለትን ቅን ሃሳብ በእብሪት ንቆ ማለፍ ሆነ፡፡
- ግድያ፣ እስራት፣ ማሳደድና ማፈናቀል፣ ድርጅቶችን ማፍረስ፣ ህግንና ህገመንግስትን በግል ፈቃድና ፍለጎት ቀይሮ፣ የፍትህ ስርአቱን፣ ሰራዊቱንና ሌላውንም ከመለስ ዜናዊና ከአገዛዙ ነጻ ሊሆኑ ይገባቸው የነበሩትን ተቋማት በመሳሪያነት በመጠቀም ተቃዋሚዎችን ለማጥፋት መንቀሳቀስ ሆነ፡፡
- ከምርጫ በኂላ መለስ ዜናዊ እንደ ትልቅ ግኝት የሚያራገበው በታወቁት የአፍሪቃ አምባገነንና ሌባ ገዥዎች በነቦካሳና በነሞቡቱ ስራ ለይ ውሎ ለህዝባቸው መከራ ያተረፈን ፖሊሲ ከወደቀበት የታሪክ ቆሻሻ አንስቶ የልማት

መንግስት ቲዎሪ (Developmental State) በሚል ስም የራሱን አገዛዝ ብቻ ልማት አምጪ አድርጎ ለማቅረብ የሚያሰራጨው ርእዮት፣

- ለሃገራችን የአንድ ፓርቲ ፍጹማዊ የበላይነት (One party hegemony) ይበጃታል በማለት ለካድሬዎቹ በስፋት መስጠት የጀመረው ስታሊናዊ ጥምቀት፤
- ይህንን የአንድ ፓርቲ ፍጹማዊ የሆነ የበላይነት ለማረጋገጥ በማሰብ፣ የሚመረጠው ሰው ከማራጩ የበለጠበት፣ የቅርብ ግዜው 4 ሚሊዮን ተመራጭ ያቀረበበት ሁኔታ፣ አገሬውን በሙሉ በተለያዩ ማስገደጃዎች ተጽእኖ እያደረገ የኢህአዴግ አባል ለማድረግ፣ በንኪኪነት ስም ህብረተሰቡን በዘር ብቻ ሳይሆን በፖለቲካም ጭምር ከፋፍሎ ለመግዛት በማሰብ አባለትን ለማሰባሰብ እየፈጸመው ያለው ጉድ፤
- የሰላማዊ ትግል ማድረጊያ ህጋዊ መብቶችን፣ የመሰብሰብ፣ የመናገር፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድርግ፣ ስራ የማቆምና ሌሎችንም አፍኖ መቀመጥ፣
- በፖለቲካ ድርጅቶች ስምና አርማ ላይ ወሳኞቹ የድርጅቶቹ አባላት ሳይሆኑ እነ መለስ ዜናዊና እነበረከት መሆናቸው፤

እነዚህና ሌሎችንም ነጥቦች በማንሳት እነዚህ ነጥቦች በሰላማዊና ህጋዊ ትግሉ ላይ ያላቸውን እንደምታ ግንቦት7 ከላይ በጠቀስኩት ሰነድ መርምሯል። እኔ ደግሞ ይህ የጠቀስኩት የግንቦት7 ሰነድ ከተጻፈ በኋላ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የወሰዳቸውን ተጨማሪ አፋኝ እርምጃዎች እንድታጠኑ እጋብዛችኋለሁ።

- ምርጫን፣ ሰብአዊና የሲቪል መብቶች የሚያስተምሩ ለእነዚህ መብቶች መከበር የሚሟገቱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን (መያዶች) ከፖለቲካ ድርጅቶች ለይቼ አላያችሁምና ከ10 በመቶ በላይ በጀታችሁን ከውጭ ማግኘት አትችሉም የሚል ህግ ማውጣት፤
- ተቃዋሚ ፓርቲዎችም በውጭ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ደጋፊዎቻቸው የገንዘብ እርዳታ እንዳያገኙ ለማድረግ ታስቦ የወጣው ህግን
- በስልጣን ለመቆየት ሲል በሃገራችንና በሁላችንም የዘለቄታ ደህንነትና ጥቅም ላይ ከፍተኛ መዘዝ የሚያስከትሉ ጉዳዮችን መፈጸም፣ ለምሳሌ ፈጽሞ ተቀባይነት ከሌለው በሱማሊያ ላይ ቀድሞ ከተካሄደው ወረራ በተጨማሪ፤ በስንት መስዋእትንት ቀደምቶቻችን ያስረከቡንን የሃገራችንን መሬት ለሱዳን አሳልፎ መስጠትን፤
- በሰሞኑን መግለጫው እንደታየው የአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ሊቀየር ይችላል ከሚል ስጋት ሀዩማን ራይት ወች ያወጣውን ዘገባ አስመልክቶ አሜሪካንን ራሷን በነገር የሚወጋ ቻይናን አቅፎ ለመተኛት መዘጋጀቱን መጠቆም፤
- በመጨረሻም ከጥቂት ቀናት በፊት እንዳየነው ተራ የመሰብሰብ መብት ለአንድነት ፓርቲ በመከልከል፣ ለእዚህ ተራ መብት መከበር ሳይቀር ድርጅቶች አማላጅ መላክ የተገደዱበትን ሁኔታ መፍጠር፤

እነዚህና ሌሎችም ያልዘረዘርናቸው ነጥቦች፣ በማያሻማ መንገድ ስለመለስ አገዛዝ የሚነግሩን ነገር አለ። የመለስ አገዛዝ የቀረው ነገር ቢኖር። "በምንም አይነት ሰላማዊና ህጋዊ ትግል የሚያደርጉ ድርጅቶች እንዲኖሩ አልፈቅድም፡ ኢህአዴግ ብቸኛው ፓርቲ ነው።" የሚል አዋጅ ማወጅ ብቻ

ነው፡፡ ይህንን አቋሙን በአዋጅ ስላላወጣ ብቻ በተግባር ይቻላል የሚል ቅዥት ማንም ሊኖረው አይገባም የሚል ድምዳሜ ግንቦት7 የሁኔታዎች ግምገማ ያደረገበት ሰነድ አካል ነው፡፡

**ቀጥሎ ግንቦት7 ያነሳው ጥያቄ; በዚህ ሁኔታ ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ምን ያስገኛል?** የሚለውን ነው፡፡ ለእዚህ ጥያቄ የሰጠነው መልስ በመያሻማ ቋንቋ ተቀምጧል፡፡

በዋንኛነት በአገዛዙ በጎ ፈቃድ ስር፣ አገዘዙ በሚያወጣውና እንዳሻው በሚሰብረው ህግና ደንብ ስር፣ የሚደረግ ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ሊኖር አይቻልም፡፡ አገዛዙ ለተወሰኑ ድርጅቶች ይህን ቀዳዳ ቢከፍትም የራሱን ምስል ለማሳመሪያ፣ መጽዋች ሃገሮችን ለመሸንገያ እንዲጠቀሙት ብቻ አድርጎ የሚቀርጻቸውና የሚቆጣጠራቸው ይሆናሉ፡፡ የራሳቸው ህልውና ኖሯቸው በ97 ምርጫ እንደታየው ስልጣኑን ሊያናጉ የሚችሉበት ደረጃ ላይ እንዳይደርሱ ምንም ነገር ለማድረግ የማይመለስ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

**በእዚህ ሁኔታ አሁን ቅንጅት የሚከተለው መስመር ያዋጣል? ወይንስ የተለየ እስትራቴጂ መቀየስ ያስፈልጋል?** የግንቦት 7 መልስ አያዋጣም፣ ሌላ ስትራተጂ መቀየስ ያስፈልጋል የሚል ሆኗል፡፡

ይህን ከመለስን በኋላ የተሸጋገርነው ወደሚቀጥለው ጥያቄ ነበር፡፡ **አዲስ እስትራቴጂ ያስፈልጋል ከተባለ ይህ እስትራቴጂ ምን መልክ ይኖረዋል?**

ለእዚህ ጥያቄ መለስ መስጠት የጀመርነው በቅድሚያ ሁላችንም ሊኖረን ስሊሚገባው የአመለካከት ጥራት በማመላከት ነው፡፡

- በቅድሚያ ወያኔ በራሱ ፈቃድ/ በልመናና በምልጃ የሚሰጠው ዴሞክራሲያዊ እድል አለሞኖሩን መረዳት፤
- ከአሁን በኋላ ይህ እድል ወያኔ በማስገድድ ወይም በማስወገድ የሚመጣ መሆኑ.መቀብል ነው
- ቀጣዩ ትግል አብዛኛውን በመለስ እብሪት የተዋረደውን፣ መለስ ዜናዊ በዴሞከራሲና በሰብአዊ መብቶች፣ በፍትህ ላይ የሚሳየውን ማላገጥ፣ በሃገርና በወገን ላይ የሚፈጽመውን ግፍና ወንጀል አምሮ ከልብ የሚቃወሙትን ሃይሎች የሚያሳባስብ፣ ሁሉንም ሊያስማማ የሚችሉ መሰረታዊ መርሆዎችን ማስቀመጥ፣ በእነዚህ መርሆዎች ዙሪያ ሰፊ ህብረት መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ መሆኑን ገልጸናል፡፡ አዲስ ስላልነውም የመተባበሪያ መርህ ስናትት የሚከተለውን አስቀምጠናል፡፡

    - ስልጣን፤ ህዝብ በነጻነት በተሳተፈበትና በወሰነበት ዴሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ አማካይነት ብቻ የሚያዝ መሆኑን፤
    - አንድ ሰው አንድ ድምጽ የሚል የኒቨርሳል የፖለቲካ መብት ያለው ሙሆኑን
    - እየአንዳንዱ ግለሰብ በህግ ፊት እኩል መብት ያለው መሆኑን
    - የሚፈጠረው ህብረት መሰረታዊ ናቸው በማለት የሚስማማባቸው መርሆዎች በስራ ላይ የሚውሉት፣ ህብረቱም እንደ ህብረት ወደ አንድ የታለመለት ግብ መንቀሳቀስ የሚችለው፣ ይህንን እንቅስቃሴ ለማድረግ የተስማማን ሃይሎች እንቅስቀሲያችን ኢትዮጵያ በምንላት አንድና ሉአላዊ ሃገር ውስጥ የሚከናውን መሆኑን መቀበል ስንችል መሆኑን የሚያሳዩት ናቸው፡፡

ከእዚህ በኋላ ግንቦት7 እንደ ድርጅትና እንዲሁም ግንቦት7 እንዲፈጠር የሚፈልገው ህብረት ምን አይነት የትግል ስልት በስራ ላይ ያውላል? የሚለው ጥያቄ ቀጥሎ ምላሽ ማግኘት የነበረበት ነበር።

ግንቦት7ም ሆነ የሚፈጠረው ትብብር/ቅንብር ሁለ ገብ የትግል ስልት በመጠቀም፣ ከሰላማዊ ህዝባዊ እምቢተኛነት እስከ አመጽ የሚደርሰውን ጨምሮ፣ የመለስ አገዛዝ ወዶ ሳይሆን ተገዶ ወደ ድርድር ይህ ካልሆነም ማስወገድ የሚቻልበትን ትግል ማካሄድ ይኖርበታል ብለናል። ይህ የግንቦት7 አቋም የተገለጸው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የሃገሪቱን መሬት ለሱዳን ከመሸጡ በፊት፣ ሁማን ራይት ዎች በኦጋዴን ግፍ ላይ ተንተርሶ በስው ዘር ላይ በተፈጸመ ግፍ አገዛዙን ሳይከሰው በፊት ነው። በበኩሌ እነዚህ የቅርብ ግዜ ወንጀሎች መሰረታዊ ጥያቄ የሚያስነሱ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። ከመለስ ዜናዊ መንግስት ጋር መደራደር የሚለው ቃል ከፖለቲካ ቋንቋችን የሚወጣው፣ መለስ ዜናዊ ምን ያህል ተጨማሪ ህዝብ ሲጨርስ ምን ያህል የሃገር መሬት ሸጦ ሲያበቃ ነው የሚል ጥያቄ እያስነሳብኝ ነው። እንዲህ አይነት ግዙፍ ወንጀሎች ከሚፈጽም አገዛዝ ጋር የሚደረግ ድርድር፣ አገዛዙ መደራደር እፈለግላሁ ቢልስ፣ በየትኛው የህግና የሞራል መመዘኛ ተቀባይነት ይኖረዋል። ይህ የኔ ጥያቄ ነው። ወደፊትም በግንቦት7 ውስጥም የሚነሳ ጥያቄ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። ወደ ትግል ስልታችን ጉዳይ  ስመለስ በተለይ ስለሰላማዊ ትግል ያለንን አመለካከት በአጭሩ አቀርባለሁ።

ግንቦት7 መለስ ዜናዊና አፋኝ በላደረቦቹ እንደፈለጉት የሚጥሱትን ህግና ህገ-መንግስት ተማምኖ የሚደረግ ሰላማዊና ህጋዊ ትግል አብቅቶለታል ብሏል። እንዲህ አይነቱ ህገዊና ሰላማዊ ትግል ቅንጅት ከምጫ 97 በኋላ በህዳር ወር በጠራው የሰላማዊ ህዝባዊ አምቢተኛነት ጥሪ ተሞክሮ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ታይቷል። የተደረገው ሙከራ አንድ ግዜ ቢሆንም ያሙከራ የመለስ አገዛዝ ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ ለሚደረግ ትግል የሚሰጠው ምላሽ ምን እንደሆነ በግልጽ ለማየት አስችሎናል። በግንቦት7 ውስጥ የተሰባሰብን ግለሰቦች ሰላማዊና ህጋዊ ትግል በማናቸውም አገዛዝ ስር፣ በማናቸውም ወቅት ይሰራል የሚል ቀኖናዊ እምነት የለንም። በኮነኔል መንግስቱ፣ በግራዚያኒ፣ በናዚዎቹ ዘመን እንደማይሰራ ሁሉ፣ ራሱን በከፍተኛ ደምና ወንጀል ባበከተ የመለስ ዜናዊ አገዛዝም ዘመንም አይሰራም ብለናል። ልብ በሉ ህጋዊ የሆነውን የሰላማዊ ትግል ማለታችን መሆኑን። ይህ አብቅቶለታል። በሌላ በኩል ግን የመለስንና የበረከት ፈቃድ ሳይጠይቅ በጥንቃቄ፣ በህቡእ በሚፈጸም አደረጃጀት፣ የመለሰን ፈቃድ የማይጠይቅ የህዝባዊ እምቢተኛነት ሰላማዊ ትግል በስራ ላይ መዋል ይቻላል የሚል እምነት ግንቦት7 እንዳለው ለማሳወቅ እወዳለሁ። ግንቦት ሰባት በሃገራችን የሰላማዊ ትግል መች ተጀመረና መች ተሞከረና ይላል። ይህ ያልተጀመረና ያልተሞከረ የትግል ስልት ተማምኖ የሚንቀሳቀሰው፣ የመለስ ዜናዊን ህግና ህገ-መንገስት ሳይሆን፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ የውጭ አምባሳደሮችን ምልጃ ጣልቃ ገብነት ተማምኖ ሳይሆን፣ራሱን በህቡእ በማደራጀት በሚፈጥረው ድርጅታዊ ብቃትና ዝግጁነት ላይ ብቻ ነው። ይህ ልዩነት መሰረታዊ በመሆኑ አድማጮቼን በጥሞና እንዲያስቡበት እማጸናለሁ። በእዚህ መንገድ፣ በሚገባ ህዝብ ያደራጀና ያሰተማረ አካል ሊገለገልባቸው የሚችልባቸው የሰላማዊ ህዝባዊ እምቢተኛነት ትግል ስልት አካል የሆኑ ዘዴዎች ብዙ ናቸው። በሃገራችን ገና አልተሞከሩም እንላለን።

ከትግል ስልቱ ጋር ግንቦት7 በግመገማው ሰነዱ ያስቀመጠው ነጥብ የንቅናቄው የፖለቲካ ግብና እንዲሁም ግንቦት7 ሁላችንም ካለንበት ችግር ለመውጣት እንድንችል ወሳኝ ነው ብሎ የሚያምነው የድርጅቶች ህብረት የፖለቲካ ግብ ምን መሆኑን እንዳለበት የሚጠቁም ነው።

- የትብበሩ የፖለቲካ ግብ፣ ስልጣን ዴሞክራሲያዊ በሆነ የህዝብ ውሳኔ መያዝ የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው። ከአሁን በኋላ ምንም አይነት ምርጫ የሚባል ነገር ከመታሰቡ በፊት ቅድሚያ ለነጻ ተቋማት ምስረታ የሚሆን የሽግግር ግዜ መፍጠር ነው።
- የነጻ ተቋማት ምስረታ ማለት፣ መከላከያውን፣ ስለላውን፣ ፖሊሱን ፣ የፍትህ ስርአቱን፣ ሚድያውን፣ የምርጫ ቦርዱን ከአንድ የፖለቲካ ፓርቲ አገልጋይነት ነጻ አድርጎ ማደራጀት ማለት ነው።

ከእዚህ በተጨማሪ ንቅናቄያችን፣ ልክ እንደ ነጻ ተቋማቱ፣ የሲቪክ ድርጅቶች፣ በተለይ ዋናዎቹ የሙያ መሃበራት፣ የአስተማሪው፣ የላብአደሩና የነጋዴው መሃበራት ፍጹም ነጻ በሆነ መንገድ የመደራጀት መብታቸው ተከብሮ በነጻነት መቋቋማቸው ከምርጫ በፊት መቅረብ ካለበት ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ አንዱ መሆን ይገባዋል የሚል ግንዛቤ ላይ ደርሷል። ይህ በግምገማ ሰነዳችን ያልተቀመጠ ቢሆን በአባሪ ሰነድነት በቅርቡ ይታከላል የሚል እምነት አለኝ። ይህ አቋም ተቀባይነት ማግኘቱ የፖለቲካ ድርጅቶች በእነርሱ ፈቃድ ብቻ የሚሰጥ የዴሞክራሲ መብት እንዲከበር ሳይሆን፣ ይህ መብት የራሱ ተቋማዊ ጥበቃ ያለው እንዲሆን ሙሉ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጡበት ቁልፍ አቋም ነው የሚል እምነት አለን። የሙያ መሃበራት አበላቱም በነጻነት እንዲደራጁ ምኞትና ለእዚህም ምኞት መሳካት ቁርጠኛ አቋም ያላቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች ከልባቸው እንዲደግፉ፣ የፖለቲካ ትግሉንም በነጻ ለመደራጀት መብታቸው ሲባል የሚደረግ ትግል አድርገው እንዲወስዱት ያበረታታቸዋል።

ከላይ የተቀመጡትንና በግልጽ የሚታዩ ነጥቦችን በሙሉ ተገንዝበን፣ በየደረጃው መፈጸም ላለባቸው ክንዋኔዎች ተግተን መስራት አንችላለን ብሎ ግንቦት7 ያምናል።

ከላይ የጠቀስናቸው የነጻ ተቋማት በተመሰረቱበት ሁኔታ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ማድረግ ይቻላል። ያኔ እኔ ከእዚህ ፓርቲ፣ በእዚህ ፖሊሲ እለያለሁ ብሎ ለመከራከር ህዝብን ለመቀስቀስ ድርጅቶች መብታቸው ይከበራል። ህዝብም የፈለገውን ይደግፋል። በምርጫ ወቅትም አማራጮች አሉትና የሚስማመውን ይመርጣል። ለፈቀደው ድርጅት የሰጠው ድምጽ በአግባቡ ይቆጠራል። አብዛኛውን ድምጽ ያገኘ ስልጣን ላይ ይወጣል። በሃገራችን ህዘብን የስልጣን ባለቤት ማድረግ ሌላ አቋራጭና ሌላ ዘዴ የለውም። አበቃ። ይህንን በማለት ረጅሙን የንገግሬን ክፍል በእዚህ እጨርሳለሁ። ቀጥሎ የማነሳው አብይ ጉዳይ፡

**ግንቦት7 ይሁን ወይም ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች የሚሰባሰው ህብረት፣ ሰላማዊና ህጋዊ ከሆኑ ድርጅቶች ጋር ምን አይነት ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል?** የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት ነው።

በመርህ ደረጃ ያስቀመጥናቸውን መሰረታዊ አላማዎች የሚቃወም፣ በሃገራችን ውስጥ በህጋዊነት የተቋቋመ ድርጅት ይኖራል የሚል እምነት ግንቦት7 የለውም። ይህ ወያኔንና ለወያኔ አገልጋይ ለመሆን ቆርጠው የተነሱና በተግባርም ይህንን ሲሰሩ ካየናቸው ድርጅቶች በስተቀር። እነዚህም የልደቱ ኢደፓና የአየለ ጫሚሶ ቡድኖች ናቸው። ድርጅት የሚለው ቃል ለእነሱ መጠቀሙ ይከብዳል። ግንቦት7 ያቀረበው ሃሳብ በስራ ቢተረጎም አብዛኛዎቹ ድርጅቶች ደስተኞች ይሆናሉ የሚል እምነት አለን። እውነት ለመናገር እንደ ልደቱ ያለውም፣ ‹ወያኔ አፋኝ ነው። ነጻ ተቋማቱ ለኔም ያስፈልጋሉ ይህንን አላማ እደግፋለሁ› ብሎ በአደባባይ ከተናገረ የሚከፋን አይሆንም። አንድ ላይ እንስራ ካለ ብቻ ነው ችግሩ። ‹አንዳንዶቻችሁ በግልም እንደጠቆማችሁልኝ ሁሉም ተቃዋሚ በኢትዮጵያ እውነተኛ ዴሞክራሲ ቢሰፍን ተጠቃሚ እሆናለሁ ብሎ ያስባል የምትሉት ቲዎሪ አይሰራም። በዴሞክራሲ ምምጣት እንጎዳለን የሚሉ መምጣቱን የማይፈልጉ ድርጅቶች አሉ›

ብላችሁናል። ይህ አይሆንም የሚል ሙግት ለመግጠም አልፈልግም። ግንቦት7 በእዚህ ላይ ያለው አቋም ግልጽ ነው። የምትጠረጥሯቸው ድርጅቶች በተግባር ሲቃወሙት እስካላየን ድረስ ለተለያዩ ምክንያቶች ይህን ሊቃወሙ የሚችሉ አሉ ብሎ መላ መምታት ለምንም አይጠቅመንም ባይ ነን። በእኛ እምነት ከእዚህ በላይ ያስቀመጥናቸውን መሰረታዊ የዴሞራሲ ዋልታ የሆኑ ተቋማትን የማቆም ሃሰብ ተቃውሞ እድሜውን ማራዘም የሚችል የፖለቲካ ተቃዋሚ በፖለቲካው ሜዳ ሊመጣ አይችልም። ጥያቄው ከፖለቲካ ድርጅቶች ህልውና ጋር የተያያዘ በመሆኑ እንደተራ ነገር ወደ ጎን ገፍተውት የሚያልፉት አይሆንም ብለን እናምናለን።

ስለዚህ በህዝብ ምርጫ ብቻ ስልጣን  መያዝና ከስልጣን ጥያቄ በፊት የነጻ ተቋማት ምስረታ ይቅደም በሚለው ጉዳይ ላይ ህጋዊ ተቃዋሚዎች የሚያነሱት ተቃውሞ አይኖርም ባዮች ነን። አንዳንዶቹ እንደ ቅንጅት የመሳሰሉት ድርጅቶች ዛሬ በተከፋፈለ ሁኔታ ቢገኙም ይህ የነጻ ተቋማት ጥያቄ መሪዎቹና ደጋፊዎቹ መስዋእትነት የከፈሉበት መሰራተዊ ጥያቄ ነው። የራሳቸው ጥያቄ ነው ማለት ነው። ነጻ ተቋማት፣ ድምጽህ እንዲከበር አስፈላጊ ናቸው። ለእነዚህ ተቋማት መፈጠር በምናደርገው ትል ከጎናችን ቁም ብሎ በሚሊዮኖች የሚቆጠርን ህዝብ ለትግል ጠርቶ፣ በሺዎች መስዋእትነት የከፈሉለትን፣ በመቶ ሽዎች የሞቆጠሩ የታሰሩበትን የተሰደዱበትን የተፈናቀሉበትን፣ መተዳደሪቸውን ያጡበትን መሰረታዊ የፖለቲካ አጀንዳ የትኞቹም ከቅንጅት የወጡ ክፋዮች ሲቃወሙት አይታየንም።  የቀድሞ የህብረት ደርጅቶችም ቢሆኑ ቅንጅትን ከ1997 በፊት ሲከሱት የነበረው ነጻ ተቋማት በሌሉበት ምርጫ ለምን ይገባል የሚል በመሆኑ፣ አሁንም እነዚህ ተቋማት የሉምና፣ በተለይ ከምርጫ97 በፊት አቅርበውት የነበረው ሃሰብ ትክክለኛነት በተረጋገጠበት ሁኔታ ሃሳቡን ተቃውመው የሚቆሙበት ሁኔታ አይኖርም። አንዳንዶቹ እንደ ኦብኮ( የኦሮሞ ብሄራዊ ኮንግረስ) ያሉት ሃሳቡን መጋራት ብቻ ሳይሆን ይህንን ሃሰብ ለማስፈጸም አመጽ የሚጠቀሙትንም ጭምር ትክክለኛነት የሚያስረዳ መግለጫ እስከመስጠት ሄደዋል። ስለዚህ በመሰረተ ሃሰቡ ላይ ችግር የለም።

ችግሩ በእዚህ ሀሳብ ዙሪያ በጋራ መስራት ይቻላል ወይ ነው። ለእዚህ ያለኝ ምላሽ ግልጽ ነው። አይቻልም ነው። አይቻልም የምለው ብዙዎቹ አይፈልጉትም ብዬ ስለማስብ አይደለም። እነዚህ ድርጅቶች የሚንቀሳቀሱበት ሰላማዊና ህጋዊ የሆነ የፖለቲካ መድረክ፣ ወያኔ ህገወጥ ብሎ ከፈረጃቸው ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመስራት የማይፈቅድ በመሆኑ ነው። እንሰራለን ብለው ቢነሱም እሩቅ ሳይሄዱ ህጋዊነታቸው ተገፎ፣ በከፍተኛ ሃገራዊ ክህደትና በዘር ማጥፋት ተወንጅለው መሪዎቻቸውንና አባላቶቻቸው ለግድያና ለረጅም ዘምን እስራት የሚዳረጉበት ሁኔታ ይፈጠራል። በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ እኛም አናደርገውም እነሱም አያደርጉትም። ይህ ማለት ግን ድርጅተዊ ግንኙነት ሳይፈጥሩ በያዙት የህጋዊ መድረክ፣ ህጋዊ ተቃዋሚዎች በአንድነት ተሰባሰበው፣ ፍትሃዊ የሆነውን የነጻ  ተቋማት ምስረታ ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም ማለት አይደለም። ይችላሉ።

በግንቦት7 እምነት በሃገራችን ከእነዚህ ተቋማት ምስረታ በላይ የገዘፈ የፖለቲካ አጀንዳ የለም። ከእዚህ በኋላ በሃገር ውስጥ ሃገዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች፣  ትግላቸው፣ ህዝብን የሚያደራጁትና የሚያስተምሩትም፣ ከማናቸውም ምርጫ በፊት በነጻ መምረጥ የሚችልበትን፣ ድምጹ መከበር የሚችልበትን፣ ህዝብ የመረጠው ስልጣን መረከብ የሚችልበትን፣ ህዝብ ያሉትን አማራጮች ምን እንደሆኑ ለማወቅ እንዲችል ተመራጮቹ ሃሳባቸውን በነጻ ሊያቀርቡለት የሚችሉበትን መብቶች ማረጋገጥና እነዚህን መብቶች የሚያስከብሩ ተቋማት እንዲመሰረቱ ትግል እንዲያደርግ ብቻ ነው።

ይህ ማለት ምንም አይነት ድርጅታዊ ግንኙነት ሳይኖረን ለአንድ አይነት ህዝባዊና ሃገራዊ አላማ በአንድነት ቆመናል ማለት ነው። በእንዲህ አይነቱ ሰፊ ህብረት ፊት የወያኔ አገዛዝ ለረጅም ግዜ ሊቀጥል አይችልም። ግንቦት7 በተደጋጋሚ የመለስን ግፈኛ አገዛዝ በቀላሉ ማስወገድ ይቻላል የሚል እምነቱ የሚመነጨው የሃገራችን ፖለቲካ ወስብሰብነቱ ተገፎ ሁሉም ዜጋና ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ሊስማሙባቸው የሚችሉ ግልጽና ቀላል የጋራ ጉዳዮች ይዞልን መጥቷል ብሎ ስለሚያምን ነው።

ግንቦት7 ህጋዊ ተቃዋሚዎች ያሉበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ስለሚያውቅ ማድረግ የማይችሉትን አድርጉ ብሎ አይጠይቅም። እነሱም በተመሳሳይ ያለንበትንና ከእነሱ የተለየ የትግል ስልት እንድንወስድ ያስገደደን ሁኔታ ተረድተው ማድረግ የማንችለውን መጠየቅ አይኖርባቸውም። ሁላችንንም ነጻ፣ ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ በሃገራችን ውስጥ እንዳንቀሳቀስ ያደረገን፣ እነሱንም ጨምሮ እያዋረደና እያበሻቀጠ ያለው፣ የነጻ ተቋማት እንዳይኖሩ አድርጎ ሃገርን እየቀጠቀጠ፣ ደስ ሲለው እየሸጠ የሚገዛው መለስ እያለ  ትግሉን ለአንዲት ሰኮንድም ቢሆን ከሌላው ህጋዊ ተቃዋሚ ወይም የመለስን እብሪት ለማስተንፈስ መስዋእትንት ለመክፈል በተዘጋጀው ሃይል ላይ ልናደርገው አይገባም። ይህ ግንዛቤና መግባባት እስካለ ድረስ በተያዩ ስብስቦች ውስጥም ሆነን ወደ አንድ የጋራ የዴሞክራሲ ጅረት ውስጥ መፍሰስ አያቅተንም።

ባለንበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ችግር በዋንኛነት ህዝብን የስልጣን ባለቤት የሚያደርግ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት መፍጠር ነው። ደግምን ደጋግመን እንዳልነው ይህ የፖለቲካ ስርአት ግንባታ የሚጀምርው በነጻ ተቋማቱ ግንባታ ነው። አንድ ድርጅት ወይም ግለሰብ የህዝብና የዴሞክራሲ ወገን መሆን አለመሆኑ በእዚህ መሰረታዊ ጥያቄ በሚወስደው አቋም በቀላሉ የሚለይ ይሆናል።

ከምርጫ 97 በኋላና አሁንም አገዛዙ እየፈጸመው ያለው ወንጀል በደንብ ላጤነ እነዚህ ነጻ ተቋማት ሳይመሰረቱ ምርጫ የማይታሰብ ነገር መሆኑን ነው። ከአሁን በኋላ በእዚህ ጥያቄ ላይ እንደ ቀድሞ ግዜ፣ እንደ1997 ምርጫ ብዥታ ሊኖረው የሚችል አካል አይኖርም። የተባሉት ነጻ ተቋማት ሳይመሰረቱ ወያኔ በራሱ ምርጫ ቦርድ፣ ፍርድ ቤትና ሰራዊት ተከቦ ስለምርጫ መግባት የሚያወራ የፖለቲካ ድርጅት ሊኖር አይገባውም። ይህንን መሰራተዊ ጉዳይ ወደ ጎን አድርገው መለስ በሚያዘጋጀው ምርጫ ለመሳተፍ የሚፈለጉ አካላት ካሉ በከፍተኛ ጥርጣሬ ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው።

እውነቱን ከሆነ የሚቀጥለው የሃገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች መሰረታዊ ልዩነት የሚያጠነጥነው፣ ትግሉንም ቀናና አጭር ወይም ረጅምና የተወሳሰበ የሚደርገው የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች በእዚህ ጉዳይ ላይ የሚወስዱት አቋም ነው። ሁሉም በመለስ አገዛዝ መብታቸው የተገፈፈና የተዋረዱ ድርጅቶችና ግለሰቦች በእዚህ ጉዳይ ላይ በፍጥነት ያላቸውን አቋም አጥርተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል። ትልቁ በፖለቲካ ድርጅቶች መሃከል የሚነሳው የመካሰስና የመወነጃጀል፣ ወያኔን ሊያስፈነጥዝ የሚልችል ሁኔታ የሚመጣው በእዚህ ጉዳይ ላይ ተቃዋሚዎች በሙሉ አንድ አቋም ያልያዙ እንደሆነ ነው። ግንቦት7 ከላይ የተቀመጡት ህዝብን የስልጣን ባለቤት ለማድርግ የሚያስችሉ መሰረታዊ ተቋማት መመስረት ወደ ጎን በማለት፣ ለፈለገው አላማ ወይም ጥቅም ወያኔ በሚያዘጋጀው ምርጫ ውስጥ ለመግባት የሚፈለጉትን በሙሉ፣ በህዝብና በሃገር መሰረታዊ የሆኑ የደህንነት፣ የብልጽግና፣ የመብት፣ የሰላምና የአንድነት ጉዳዮች ላይ የሚያሾፉ አድርጎ እንደሚያያቸው ከአሁኑ ለሁሉም ግልጽ ማድረግ ይወዳል። የነጻ ተቋሚቱን ጥያቄ ጥያቂያቸው

የሚያደርጉትን ድርጅቶች ግን በሻማ እፈላለገ ትንሽ ትልቅ ሳይል፣ መደረግ ያለበትን በሙሉ በማድረግ በህበረትና በአንድነት አብሯቸው ለመቆም ቃል ገብቷል።

በመጨረሻ የማነሳው አብይ ነጥብ፤ **በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ የተሰባሰቡ አባላትና ደጋፊዎች የስራ ድርሻ ምን መሆን አለበት?** የሚል ነው።

እዚህም ላይ ስለሃለፊነትና ድርሻ ከማውሳቴ በፊት ከሁሉም ድርጊት በፊት መቅደም በሚገባው የፖለቲካ ግንዘቤ ላይ ጥቂት ሰኮንዶች ማጥፋት እፈልጋለሁ።

- የወቅቱ ወሳኝ ሃገራዊ የፖለቲካ አጀንዳ ምንድ ነው? በሚለው ጉዳይ ላይ ግልጽ መሆን፣
- ዋናው ጥያቄ ከአሁን በኋላ ህዝብን የስልጣን ባለቤት የሚያደርግ ምርጫ በሃገራችን እንዴት ማካሄድ ይቻላል የሚለው ጥያቄ መሆኑን መረዳት፣
- ሁሉንም ዜጋና ድርጅቶች በእኩልነት የሚያስተናግድ ከምርጫ በፊት መቅደም የሚገባው የዴሞክራሲያዊ ስርአት መሰረት ሳይጣል ህዝብን የስልጣን በላቤት ማድረግ እንደማይቻል መረዳት ያስፈልጋል እላላሁ።

የድርጅቶች አባላትና ደጋፊዎች ይህንን ከተረዱ የሚቀጥለው ስራቸው ቀላል ነው።

- በቅድሚያ ድርጅታቸው ዋናውን ሃገራዊ የፖለቲካ አጀንዳ፣ አጀንዳው አድርጎ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። ድርጅታቸው በዋንኛውና ወሳኝ በሆነው የፖለቲካ አጀንዳ ላይ አቋም ካልወሰደ፣ በአፋጣኝ ግልጽ አቋም እንዲይዝ ማድረግ ይኖርባቸዋል።
- የሁሉም የድርጅት ደጋፊዎችና አባላት በመተባበር ይህ አቋም በሁሉም ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ነኝ በሚሉ ድርጅቶች ተቀባይነት እንዲኖረው ተግተው ሊሰሩ ይገባል።
- አባላት ይህንን መሰረታዊ ሃሳብ የማይቀበሉ ድርጅቶችን ላለመደገፍ መወሰን ይኖርባቸዋል።
- ባለንበት ወቅት የተለያዩ ድረጅቶች አባላትና ደጋፊዎች ገንዘባቸውን ጉልበታቸውን እውቀታቸውን ከምርጫ በፊት የተቋማቱ ምስረታ መቅደም አለበት ለሚሉ ትብብሮች ድጋፍና እነዚህ ትብብሮች ካልተፈጠሩ እንዲፈጠሩ፣ ከተፈጠሩ ደግሞ እንዲጠናከሩ በማበረታት ስራ ላይ ማዋል ይገባቸዋል።

**ንግግሬን ወደ ማጠቃለሉ ልሂድ።**
ዛሬ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች የመለስን አገዛዝ በስልጣን ጥያቄ ላይ ሊፈትኑት ከሚችሉበት ድንበር ውጭ እንዲቆሙ በመለስ ተደረረገዋል። በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ ለአንድ ድርጅት ጭፍን በሆነ መንገድ ከሚሰጥ ድጋፍ የበለጠ፣ ሃገራዊና እርባና ያለው ስራ የሚሰራው በቅድሚያ የሁሉንም ድርጅቶችና የሁሉንም ዜጎች በነጻ የመደራጀትና የማደራጀት መብት ለማስከበር በሚደረግ ትግል ላይ ብቻ መሆኑን ሁሉም ሊረዳ ይገባዋል።

የእያንዳንዱ ድርጅት አባላትና ደጋፊ በራሱ ድርጅት ላይ የቤት ስራውን ከሰራ፣ ከአባላትና ከደጋፊዎች እርዳታ ውጭ ህልውና የሌላቸውን ድርጅቶች አስገድዶ የዴሞክራሲ ትግሉ አካል እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል። የዴሞክራሲ ትግሉ ደግሞ ግልጽ የሆኑ ቀላል አጀንዳዎች ያሉት ሆኗል። በእዚህ መንገድ ከተሄደ፣ በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ዜጎች የሚደገፍ የበርካታ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ መሃበራት ቅንበር መፍጠር ይቻላል።

ቅንብር ነው ያልኩት ልብ በሉ። ውህደት፣ አንድነት፣ ቅንጅት፣ ግንባር አላልኩም።

ቅንብር ሁሉም የራሱን ድርጅታዊ ማንነት፣ ፍልስፍና እና ፖሊሲ እንደያዘ መሰራተዊ ናቸው ባልናቸው ለሁሉም በእኩልነት በሚያገለግሉ ነጥቦች ዙሪያ የጋራ አቋም መያዝ፣ ይህንን አቋም በሚመለከት ብቻ ለግዜው ተቀናብሮ መስራት መጀመር ማለቴ ነው። ከእዛ በላይ የሚያድግ ህብረት፣ ለግዜው በእዚህ ከጀመርን በራሱ ሂደት መምጣቱ ስለማይቀር ዛሬ ሊያስጨንቅን አይገባም።

ይህ ቅንብር ከሌሎች ከእዚህ ቀደም ከምናውቃቸው ሳይዘሩ ከረገፉ ሳይወለዱ ከሞቱ ህብረቶች፣ ግንባሮችና ቅንጅቶች እጣ እንዴት ሊኖረው ይችላል የሚል ጥያቄ በአእመሮዎቻችሁ እንደሚመላለስ ይሰማኛል። ለእዚህ ያሉኝ ምላሾች ቀላል ናቸው። እንዲፈጠር የምንፈልገው ቅንብር ከእዚህ ቀደም ከናውቀው ህብረት የሚለየው በጣም ቀላል በሆነ፣ በምንም መንገድ ሊያጫቃጭቅ በማይችል ግልጽ አጀንዳ ዙሪያ የሚቆም በመሆኑ፣ ከአጀንዳ ውስብስብነት የተነሳ ከሚመጣ የሁላችሁም ስጋት ከሆነው ከተለመደው መፈረካከስ ነጻ ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

እንደ ቀድሞው የቅንበሩ መሰባሲያ ዋንኛው አላማ በልሂቃን መሃል በሚደረግ ስምምነት ስለሚያዝ ስልጣን ለመዶለት ሳይሆን፣ ህዝብን የስልጣን በላቤት ለማድረግ ግልጽ በሆነ አጀንዳ ላይ ስለሚሆን ህዘብን ከመቼውም ይበልጥ ለስልጣን የሚያቀርብ ሁኔታ ይፈጠራል እላላሁ። ቀደም ብዬ ያቀረብኩት የአባላትና የዜጎች ተሳትፎ በተግባር ከዋለ፣ የእዚህ አጀንዳ ባለቤቶች የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች ሳይሆኑ የድርጅቶቹ አባላትና ደጋፊዎች፣ እንዲሁም የትኛውንም ፓርቲ ለመደገፍ ፈቃደኛ ያልሆነ በርካት መብቱ እንዲከበር የሚፈልግ ዜጋ ከሆነ፣ ድርጅቶች ይሁኑ መሪዎች በቀላሉ ሊያጥፉት የማይችሉት ጉዳይ ይሆናል። በመሪዎች ነጻ ለመውጣት ከሚፈልገው ወገን የበለጠ እራሱን ነጻ ለማውጣት ግዴታ ያለበት መሆኑን የተገነዘበ ዜጋ ቁጥሩ ጨምሯል የሚል እምነት ስላላኝ ይህም ሌላው ዋሰትና ነው። በግልጽ በአደባባይ የፖለቲካ ድርጅቶችና መሪዎች በህዝብና በአባላት ፊት በተጋባ ቃል ኪዳን ታስረው ግልጽ በሆነው የህዝብ አጀንዳ ላይ በጋራ የጀመሩትን ትግል በቀላሉ ዳቦ ተቆረሰ ጨዋታ ፈረሰ ብለው እንዳይሄዱ ማድረግ ትችላላችሁ።

ይህ ሰምምነት ተገኝቶ አንድ አይነት አቋም መውሰድ ከተቻለ ቴክኒካዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሊነሳ የሚችለውን ችግር በቀላሉ ማለፍ ይቻላል። እነዚህ ቴክኒካዊ ችግሮች ምንድን ናቸው የሚለው ርእስ፣ ራሱን የቻለ ትልቅ አጀንዳ በመሆኑ በሌላ ግዜ እንመለስበታለን። በኔ እምነት ግን ሃገራችንን ያለችበት አጅግ አሳዛኝና አሳፋሪ ሁኔታ የሚያበግነው፣ ካለፉ ጥፋቶችና ውድቀቶች ትምህርት የተማረው ሃገሩንና ወገኑን የሚወደው ዜጋ ብዙ ነው የሚል እምነት ስላለኝ የቀረበውን ሃሳብ በቀላሉ በስራ ለመተርጎም የሚያስቸግረን አይሆንም የሚል እምነት አለኝ።

ግንቦት7 ትልቁ ጥንካሬው ይቻላል በሚል እምነት የተሳሰሩ፣ ቀድመው ያለፉበትን፣ አሁን የሚገኙበትን ሁኔታ መገምገም የሚችሉ፣ ስህተትና ጥፋታቸውን ማረምና ማስተካከል ነውር አድርገው የማያዩ፣ ስለሚደርሱበት ግብ ተጨንቀው የሚያስቡ፣ ሃሳባቸውን በግልጽ ለወገኖቻቸው ለማስረዳት የማይታክቱ፣ ከወገናቸው ጋር መታገል ነጻ ለማውጣት ሳይሆን አብረው ነጻ ለመውጣት ፍላጎት ያለቻው ግለሰቦች የፈጠሩት ንቅናቄ በመሆኑ በጋራ ለሚደረገው ትግል የራሱን ድርሻ ይወጣል የሚል እምነት አለኝ። ይህ የግንቦት7 ህልም እንዲሳካ ተቀላቀሉን፣ አብራችሁን ስሩ፣ ደግፉን አበረታቱን።

እስካሁን የተናገርኩት ቁልፍና ወሳኝ በሆነ የፖለተካ አጀንዳ ላይ ቢሆንም፣ በእዚህ አጀንዳ ላይ የጋራ መግባባት መፍጠር ከተቻለ ቀጥሎ ሌሎች ቴክኒካዊ ቢሆኑም አስቸጋሪ ወደሚሆኑ ጉዳዮች

መሸጋገራችን አይቀርም ብያለሁና፣ ለእነዚህም ዝግጅቱ ካሁኑ መጀመር አለበት ብዬ ስለማምን ሁላችሁም እንድታስቡባቸው፣ አቅሙ ያለችሁም ጥናት እንድታደርጉባቸው የሚቀጥሉት ጥያቄዎች አቀርባለሁ።

ለስልጣን ፍክክር ከመደረጉ በፊት ነጻ ተቋማቱ መቅደም አለባቸው ብለናልና ተቋማቱ በሚፈጠሩበት ወቅት ስልጣን በማን እጅ ይሆናል?

ኢትዮጵያን በመሰለ ዘውገ ብዙ፣ የሃይማኖት የባህል የቋንቋ የአመራረት የአኗኗር ስብጥር ባለበት ሃገር ውስጥ፣ እንዴት የሁሉንም ፍላጎትና የጥቅም ስብጥር ያስማማ፣ ሁሉም ገለልተኛ ነው ብለው የሚያምኑት ነጻ የመከላከያና የደህንነት የፍትህና ሌሎችንም ነጻ ተቋማት ማቋቋም ይቻላል?

ለእነዚህ ተቋማት መቋቋም ቅድሚያ ተሰጥቶ፤ ለነሱ መቆም ደፋ ቀና በሚባልበት ወቅት፣ መለስ ባህገራችን ላይ የሚፈጽመውን ወንጀል እንዴት መከላከል እንችላለን? ይህ ወንጅል ሃገርን የመግደል የመበተንና የመቸርቸር ወንጀል፣ ለምሳሌ ለሱዳን እንደሸጠው የሃገራችን መሬት ማለቴ ነው።

እንዲህ አይነቶቹ አንገብጋቢ ጉዳዮች ሲነሱ ዋና ባልነው የፖለቲካ አጀንዳ ዙሪያ እንዲሰባሰቡ የምንፈልጋቸው የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲህ አይነቶቹን ጉዳይ ማስተናገድ የሚችሉበት ምን ሜካኒዝም ሊኖራቸው ይገባል?

ስለዴሞክረሲና ስለህዝብ የስልጣን ባለቤትነት ስናወራ፣ ዴሞክራሲ የሚሰፍንበት፣ ስልጣን በህዝብ የሚያዝበት ሃገር ሊያሳጣን የመለስ አገዛዝ ቀን ተሌት ተግቶ በመስራት ላይ በመሆኑ፣ ይህንና ተመሳሳይ ሌሎችንም ጉዳዮች ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸው በሁሉም ድርጅቶች የሚታዩበት ሜካኒዝም በአስቸኳይ ሊፈጠር አይገባውም ወይ?

ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

አንዳርጋቸው ጽጌ
ለንደን ሰኔ 2000 አ.ም